# የመሰረታዊ የንግድ ዕቃዎች ለህበረተሰቡ ለማሰራጨት ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 552/2013

Revised Guidelines for Distribution of Basic Commercial Goods to the Community (Directive No. 552/2013)


የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

Ministry of Trade and Regional Integration



ግንቦት 1፥ 2008

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ንግድ ሚኒስቴር፣ ከመሰረታዊ የንግድ ዕቃዎች መሀከል ለህብረተሰቡ ለምግብ ፍጆታ ከሚውሉት ሸቀጦች ስኳር፣ ፖልም የምግብ ዘይት፣ ስንዴና የስንዴ ዱቄት ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ የታየባቸዉን እና ይኸው ክስተት በህብረተሰቡ የእለት ተዕለት ኑሮ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያስከተሉትን በጥናት በመለየት ግብይታቸውና ስርጭታቸው ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ጠቀሜታ እንዳለው የታመነበት በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በኑሮ ውድነት የተነሳ በህብረተሰቡ ላይ የደረሰውን ተጽእኖ ለመቀነስና ገበያውን ለማረጋጋት ሲል በከፍተኛ ዋጋ ገዝቶ በድጎማ በዝቅተኛ እና በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ላሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ለማሰራጨት የሚያቀርባቸውንና ቀደም ሲል ያሰራጫቸውን የምግብ ፍጆታ ሸቀጦች ለታለመላቸው ዓላማ እንዲውሉ ለማስቻል በፌዴራል መንግስቱ፣ በክልል መንግስታት፣ ተጠሪነታቸው ለፌዴራሉ መንግስት በሆኑ የከተማ አስተዳደሮች እና በመላ ሀገሪቱ በተዋረድ በሚገኙ የመንግስት አስተዳደር እና ሌሎች አካላት ጨምሮ ሸቀጦቹን በመግዛት፣ በመሸጥ ፣ በማጓጓዝ፣ በማከማቸት ለህብረተሰቡ በማሰራጨትና መሰል ተግባራት ሂደት ውስጥ ስለሚኖራቸዉ ድርሻና ኃላፊነት ወጥነት ያለው የአፈፃፀም፣ የክትትል፣ የድጋፍ አሰጣጥና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ንግድ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ የመመሪያው አካሄድ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ከመሰረታዊ የንግድ ዕቃዎች መሐከል ስኳር፣ ፓልም የምግብ ዘይት፣ ስንዴና የስንዴ ዱቄት ለህብረተሰቡ ለማሰራጨት ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 552/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ዓላማ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት፣ በየጊዜው በህብረተሰቡ ላይ የሚታየው የኑሮ ውድነት በህብረተቡ ላይ እያሳደረ ያለውን ተፅእኖ ለመቀነስ እና ገበያውን ለማረጋጋት ሲል በከፍተኛ ዋጋ ገዝቶ በድጐማ በዝቅተኛ እና በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ላሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ለማሰራጨት የሚያቀርባቸውንና ቀደም ሲል ያሰራጫቸውን የምግብ ፍጆታ ሸቀጦች በታለመላቸው ዓላማ መሰረት ለሸማቹ ህብረተሰብ እንዲደርስ በማድረግ የድጐማው ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡

3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት የንግድ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡
2. "ክልል" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን ማለት ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደርንም ይጨምራል፣ እንዲሁም በንግድ ሕጉ "ጠቅላላ ግዛት" የሚለው "ክልል" ተብሎ ይነበባል፣
3. "መሰረታዊ ሸቀጥ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት መሰረታዊ የንግድ ዕቃዎች መሐከል ስኳር፣ ፓልም የምግብ ዘይት፣ ስንዴና የስንዴ ዱቄት የሚባሉትን ከሸማቾች የየዕለት ፍላጐት ጋር የተገናኘ የንግድ ዕቃዎች እና ሚኒስትሩ በጥናት በመለየት ግብይታቸውና ስርጭታቸው ላይ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሸቀጦች ናቸው፡፡
4. "ቢሮ" ማለት የክልል ንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ወይም ሌላ የሚመለከተው ቢሮ ወይም የክልል ኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡

5. "የመንግስት የልማት ድርጅት" ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 ዓ.ም የተሰጠው አጠቃላይ ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት የምግብ ፍጆታ ሸቀጦችን በማሰራጨት ሂደት ተሳታፊ የሆኑት የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት (አለ በጅምላ) እና የስኳር ኮርፖሬሽንን ብቻ ይይዛል፣

6. "የዱቄት ፋብሪካ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት ስንዴን ገዝቶና ፈጭቶ የስንዴ ዱቄትን ለጅምላ ወይም ለቸርቻሪ ነጋዴ ወይም ለዳቦ ቤት በቀጥታ ለማከፋፈል በትስስሩ ውስጥ የተካተቱ በመንግስት ወይም በግል ባለቤትነት የተቋቋመ ድርጅት ነው፣

7. "ችርቻሮ ሻጭ" ማለት በንግድ አሰራርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 የተሰጠው አጠቃላይ ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት መሰረታዊ ሸቀጦችን በማሰራጨት ሂደት ተሳታፊ የሆኑትን ብቻ ይመለከታል፡፡

8. "ሸማች" ማለት በንግድ አሰራርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 የተሰጠው አጠቃላይ ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት መሰረታዊ ሸቀጦችን ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ ፍጆታ የሚገዛ የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

9. "የህብረት ስራ ማህበራት" ማለት በህብረት ስራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር -147/1991 ዓ.ም የተሰጠው አጠቃላይ ትርጉም እንደተተበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት ከመሰረታዊ የንግድ እቃዎች መሀከል ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ የታየባቸው እና በህብረተሰቡ የየዕለት ኖሮ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከተሉ የምግብ ፍጆታ ሸቀጦችን በማሰራጨት ሂደት ተሳታፊ የሆኑትን ብቻ ይይዛል፣

10. "የሸማች ህብረት ስራ ማህበራት" ማለት በህብረት ስራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር -147/1991 ዓ.ም ተሰጠው አጠቃላይ ትርጉም እንደተተበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት ከመሰረታዊ የንግድ እቃዎች መሀከል ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ የታየባቸው እና በህብረተሰቡ የየዕለት ኖሮ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከተሉ የምግብ ፍጆታ ሸቀጦችን በማሰራጨት ሂደት ተሳታፊ የሆኑትን ብቻ ይይዛል፣

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

11. "አስተዳደራዊ እርምጃ" ማለት ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት ሲባል እንደ አስፈላጊነቱ ህግ ተላልፈው በሚገኙ አስመጪ/አቅራቢ ድርጅቶች፣ ህብረት ስራ ማህበራት ዩንየኖች፣ የመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት፣ ዱቄት ፋብሪካዎች፣ ቸርቻሪ ነጋዴዎች ወደ ህግ ከመወሰዱ በፊት ነጋዴው ጥፋቱን አውቆ ተፀፅቶ እንዲታረም ወይም በከፊልና በሙሉ ከሂደቱ የሚታገድበትን የሚጨምር በየደረጃው የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ነው፡፡

12."'አገልግሎት ሰጪ" ማለት በአዋጅ 686/02 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት መሰረታዊ ሸቀጦችን በግብአትነት ተጠቅሞ እሴት በመጨመር በቀጥታ ለህብረተሰቡ ምርቱን ወይም አገልግሎቶቹን የሚያቀርብ የንግድ ተቋም ሆኖ ለዘይት እና ስንዴ ዱቄት ስርጭት ማንኛውንም ሪዞርቶች እና ባለ ኮከብ ሆቴሎችን አያካትትም፡፡

13."ግብረ ሀይል" ማለት ከመሰረታዊ የንግድ እቃዎች መሀከል ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ የታየባቸው እና በህብረተሰቡ የየዕለት ኑሮ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከተሉ የምግብ ፍጆታ ሸቀጦችን በዚህ መመሪያ መሰረት የክትትል፣ ድጋፍ አሰጣጥና ቁጥጥር ተግባራትን ለማከናወን ከፌደራል መንግስቱ እንስቶ በመላ ሀገሪቱ በተዋረድ በሚገኙ በመንግስት አስተዳደር እርከኖች ደረጃ የሚቋቋም አካል ነው፡፡

14."ዳቦ ጋጋሪ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የስንዴ ዱቄት ትስስር ከተፈጠረላቸው ዱቄት ፋብሪካዎች ገዝቶ በመጋገር በተተመነው ዋጋና መጠን ልክ ለሸማቹ ወይም ለቸርቻሪ የሚሸጥ ድርጅት ነው፡፡

15."ዳቦ ቤት" ማለት በዚህ መመሪያ በተፈጠረው የስርጭት ትስስር መሰረት በራሱ ድርጅት ጋግሮ ወይም ከዳቦ ጋጋሪ ገዝቶ ዳቦ ለሸማቹ የሚሸጥ ወይም የሚቸረችር ንግድ ተቋም ነው፡፡

16. አስመጪ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የፓልም ምግብ ዘይት ወይም ጥሬ ስንዴ ወይም ስኳር የተባሉትን የንግድ እቃዎች በየብስ ወይም በባህር ወይም በአየር ከውጪ ወደ ውስጥ የሚያስመጣ ህጋዊ ሰው/ነጋዴ ነው፡፡

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1. ይህ መመሪያ የግብረ ሀይል ኮሚቴዎች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪዎች/አቅራቢዎች፣ የህብረት ስራ ማህበራት ዩንየኖች፣ የዱቄት ፋብሪካዎች፣ ዳቦ ጋጋሪዎች፣ ዳቦ ቤቶች፣ ህብረት ስራ ማህበራት፣ ችርቻሮ ሻጮች፣ የሸማች ህብረት ስራ ማህበራት እና ሸማቾች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2. ይህ መመሪያ በሚከተሉት አካላትና የምግብ ሸቀጦች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፣

2.1. ስንዴ ከመንግስት ሳይሆን ከነጻ ገበያ የሚገዙና በስርጭት ትስስር ውስጥ ያልተካተቱ የዱቄት ፋብሪካዎች እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች፣ ብስኩት ፋብሪካዎች፣ ጣፋጭ ምግብ ቤቶች፤

2.2. መንግስት አምርቶትም ይሁን ከውጭ ገዝቶና ዋጋ ተምኖ ከሚያሰራጫቸው ውጭ ያሉ ሸቀጦች ላይ የተሰማሩ ንግድ ድርጅቶችን፣ ነጋዴዎችን፤

2.3. የCrude RBD ድፍድፍ/ያልተጣራ ፓልም ዘይት እንዲያመጡ ተፈቅዶላቸው በራሳቸው ከውጪ አስመጥተው ለሌሎች ምርቶች በግብአትነት ለመጠቀም የተዘጋጁ ምርቶች (shortening) ላይ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ አይሆንም፤

2.4. የፓልም የምግብ ዘይት ያልሆኑ ሌሎች የምግብ ዘይት ዓይነቶች ከቅባት እህሎች፣ ከአኩሪ አተር እና ሌሎችም የሚገኙ የምግብ ዘይት ዓይነቶችን አምራች፣ አከፋፋይ፣ ቸርቻሪዎች ላይ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ አይሆንም፤

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

# ክፍል ሁለት

## 2. የግብረ ሀይል ስለማቋቋም፣ ተግባርና ኃላፊነት

### 2.1. ግብረ ሀይል ስለ ማቋቋም

በፌደራል መንግስት፣ በክልል እና በመላ ሀገሪቱ በተዋረድ የሚገኙ በዞን፣ በክፍለ ከተማ፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳና እንደ አስፈላጊነቱ ከወረዳ በታች ባሉ በመንግስት አስተዳደር አካላት ደረጃ ይቋቋማል፡፡

### 2.2. ስለ ግብረ-ኃይል አባላት

1. የፌዴራል መንግስት ግብረ-ኃይል ኮሚቴ አባላት

ሀ/ የንግድ ሚኒስቴር......................................................................................ሰብሳቢ

ለ/ የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን............................................ አባል

ሐ/ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር.............................................................አባል

መ/ የኢትዮጵያ የምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን........................................አባል

ሠ/ የሁሉም የክልል ንግድ ቢሮዎችና ከተማ አስተዳደሮች ኃላፊዎች .......................አባል

ረ/ የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎት ...................................አባል

ሰ/ የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ.....................................................................አባል

ሸ/ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን.......................................................................አባል

ቀ/ የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች......................................................አባል

በ/ የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት.....................................................................አባል

ተ/ ስኳር ኮርፖሬሽን..........................................................................................አባል

ቸ/ የመረጃና ደህንነት ኤጀንሲ..............................................................................አባል

2. የክልል/ከተማ አስተዳደር ግብረ ሀይል አባላት

ሀ/ የክልል/ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ................................................................ሰብሳቢ

ለ/ የክልል/ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ...............................................................አባል

ሐ/ የክልል/ከተማ አስተዳደር ፖሊስ........................................................................................አባል

መ/ የክልል/ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ.......................................................................አባል

ረ/ በክልሉ ወይም ከተማ አስተዳደሩ የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪዎች......................አባል

ሰ/ በክልሉ ወይም ከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ የእህል ንግድ ቅርንጫፍ ማዕከላት ...............አባል

ሸ/ የክልል/ከተማ አስተዳደር ህ/ስ/ማ ማስፋፊያና ማደራጃ ኤጀንሲ ሃላፊዎች.........................አባል

ቀ/ የክልል/ከተማ አስተዳደር የተመረጡ ዱቄት ፋብሪካ ባለቤቶች............................................አባል

3. የዞን/ከተማ አስተዳደር / ክፍለ ከተማ ግብረ ሀይል አባላት

ሀ/ የዞን/ከተማ አስተዳደር/ክፍለ ከተማ ንግድ ጽ/ቤቶች.................................................ሰብሳቢ

ለ/ የዞን ህብረት ስራ ኤጀንሲዎች.......................................................................... አባል

መ/ በዞን/ከተማ በፓልም የምግብ ዘይት እና ስኳር ክፍፍል ተሳታፊ የሆኑ የሸማች ህ/ስ/ማ ዩንየኖች፣ መሰረታዊ/ህ/ስ/ማማህበራት፣.......................................................................አባል

ሠ/ የእህል ንግድ ድርጅት ቅርንጫፍ ማከፋፈያ ማዕከላት.............................................አባል

# 4. የወረዳ ግብረ ሀይል አባላት

በቢሮዎች እንደየ ክልላቸው እና ከተማ አስተዳደሮች ተጨባጭ ሁኔታ ተገቢነት ያላቸው አካላትን ያካተተ የወረዳ ግብረ ሀይል ኮሚቴዎች እንዲቋቋም ያደርጋሉ፡፡

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

## ክፍል ሶስት

## 3. በመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦትና ስርጭት ውስጥ ያሉ ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 3.1. ንግድ ሚኒስቴር

- የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት፣ ክፍፍልና ስርጭት እንዲኖር ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮችን ባሳተፈ ሁኔታ መረጃ ይሰበስባል፣ የማስፈፀሚያ እቅድ ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

- አስመጪዎች/አቅራቢ ድርጅቶች ከግሉ ዘርፍ የሚመረጡበትን መስፈርቶች ያዘጋጃል፣ ይመለምላል፣ ያሰማራል፤

- የመሰረታዊ ሸቀጦች ግዢ እንዲካሄድ ለአስመጪዎች/አቅራቢ ድርጅቶች ከሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እንዲያገኙ ያስተባብራል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

- የአስመጪዎች፣ ቸርቻሪዎችን የሥርጭት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ በተተመነው ዋጋ መሰረት መሸጡን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤

- የአለም አቀፍ እና የሀገር ውስጥ የመሰረታዊ ሸቀጦች የመግዣ ዋጋን መሰረት በማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ በየግማሽ ዓመቱ ወይም ባነሰ ጊዜ የዋጋ ግንባታ ያደርጋል፣ ለአስመጪዎች/አቅራቢ ድርጅቶችና ለቸርቻሪ ነጋዴዎች የመሸጫ ዋጋና የትርፍ ምጣኔን ይወስናል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ለህብረተሰቡ እና ለተዋናዮች በህዝብ ማስታወቂያ ያሳውቃል፤

- ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመትና ዓመታዊ እቅዶችን፣ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለግብረ ሃይሉና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ያቀርባል፤

- የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች የሚያስመጡትን የፓልም የምግብ ዘይት አይነት እና የጥራት ደረጃ ይለያል፣ ይወስናል፣

- የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች የሚያስመጡትን የፓልም የምግብ ዘይት መጠን፣ በፓኬጅ ባለ (3 ሊ፣5ሊ፣10ሊ፣20ሊ፣25ሊ) ይወስናል፤

- የመሰረታዊ ሸቀጦች ከተቀመጠው የሥርጭት ሥርዓት ውጭ በሚያከማቹ፣ በሚያጓጉዙና በሚያሰራጩ አስመጪዎች/አቅራቢ ድርጅቶች፣ ቸርቻሪዎች ላይ የእርምት አስተዳደራዊ ወይም ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

- የክልልና የከተማ አስተዳደሮች የመሰረታዊ ሸቀጦች መጠን/ኮታ ይደለድላል፣ የአስመጪ/አቅራቢ ድርጅቶች የሚያከፋፍሉባቸውን አካባቢዎች ይወስናል፣ ያሳውቃል፤

- በግብረ-ኃይሉ ኮሚቴ የሚደረሰውን የውሳኔ ሀሳቦች ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፤

- ስርጭቱንም በሚመለከት የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን በየሶስት ወሩ ከክልል የንግድ ቢሮዎች ጋር ይገመግማል፤

- በአቅርቦትና ስርጭቱ ዙሪያ ለሚከሰቱ ችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያመላክቱ የዳሰሳ ጥናት ያከናውናል፤

- ስርጭት መዛባት ካለም ወቅታዊ እርምት እንዲወስድ ያደርጋል፣ መዛባቱን ምንጭ ከኪራይ ሰብሳቢነት ጋር ከተያያዘ በቂ መረጃ በመያዝ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፣

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዛግብ ቤት

## 3.2. የክልል/ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ

- ከሚንስቴር መስሪያ ቤቱ በሚተላለፈው የመሰረታዊ ሸቀጦች ሥርጭት አፈጻጸም መመሪያ እና በሚመደበው ኮታ መሰረት ሸቀጦቹን እስከ ሸማቹ ህብረተሰብ ሊደርስ የሚያስችል የስርጭት አፈጻጸም፣ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዐት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙንም በየደረጃው በሚቋቋመው ግብረ-ኃይል ኮሚቴ መሰረት ይከታተላል፤

- በክልሉ/ከተማው አስተዳደር የመሰረታዊ ሸቀጦች የሚሰራጭላቸውን ከተሞች /ዞኖች/ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ማከማቻና ማሰራጫ ማዕከላትን ይለያል፤ በተገቢው ጊዜና መጠን ክምችት መያዙንና መሰራጨቱን ክትትል ያደርጋል፤

- ለክልል ግብረ-ኃይል ኮሚቴ የስርጭት መረጃና የአፈፃፀም ሪፖርት ለግብረ-ኃይሉ በጹሑፍ ያቀርባል፤

- ለክልሉ ወይም ለከተማ አስተዳደሩ የተደለደለውን መሰረታዊ ሸቀጦች በክልሉ ለሚገኙ ዞኖችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም የመንግስት ተቋማት ይደለድላል፣ ያሳውቃል፤

- በዞኖች/ከተማ አስተዳደሮች የተመረጡ ሸማች ማህበራትና ቸርቻሪ ነጋዴዎችን ከተጠቃሚው ህብረተሰብ፣ እንዲሁም ዱቄት ፋብሪካዎችን ከተመረጡ ዳቦ ቤቶች ጋር ትስስር ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤

- በየወሩ የመሰረታዊ ሸቀጦች ክፍፍልና ስርጭት በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት፣ በተተመነው ዋጋ መሰረት መፈፀሙን ይከታተላል፤ ከተዘረጋው አሰራር ስርዓት ውጭ በሚያከማቹ፣ በሚያንገላቱና በሚያከፋፍሉ ሸማች ህ/ስ/ማ እና ቸርቻሪ ነጋዴዎች ላይ በየደረጃው አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

- ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የአፈፃፀም ሪፖርት በየወሩ ይልካል፤

- የንግድ ሚኒስቴር ባስቀመጠላቸው የመሰረታዊ ሸቀጦች የመሸጫ ዋጋን መነሻ በማድረግ እና እንደየርቀታቸው የትራንስፖርት ዋጋን መሰረት በማድረግ በስሩ በሚገኙ ከተማዎች የሚኖረውን የመሸጫ ዋጋ ይወስናል፣ ሥራ ላይም እንዲውል ያደርጋል፤

- በክልል ግብረ ኃይል ኮሚቴ ውስጥ በሰብሳቢነት ይሳተፋል፤ ተገቢውንም የስርጭት መረጃ ለግብረ-ኃይሉ በጽሁፍ ያቀርባል፤

- ከፋብሪካ እስከ ዳቦ ጋጋሪውና ሸማች ህብረት ስራ ማህበራት ያለው ዱቄት ፍሰት መቆጣጠር ሚያስችል መረጃ መያዙን ያረጋግጣል ለዚህም ራሱን የቻለ የክትትልና ቁጥጥር ሥርአት ይዘረጋል፤

- በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ላይ የተመሰረተ ሽያጭ መፈጸሙን፣ በተተመነው ዋጋ መሰረት እየተከፋፈለ መሆኑን፣ ፋብሪካዎች የወሰዱት የስንዴ መጠን፣ ያመረቱትንና የሸጡት የዱቄት መጠን የሚፈለገውን ውጤት ማስገኘቱን ይቆጣጠራል፤ ዳቦም በተፈለገው ዋጋና መጠን እና የስንዴ ዱቄት ለህብረተሰቡ ለሽያጭ መቅረቡን የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋሉ፤

- ለፋብሪካዎች የሚሸጥ ስንዴም ሆነ ከፋብሪካዎች እጅ የሚወጣ ዱቄት በህገ ወጥ መንገድ ወደ ጎረቤት ሀገሮች እንዳይወጣ ቁጥጥር ስርርዓት በመዘርጋት ክትትል ያደርጋል፤
- በግብረ-ኃይል ስብሰባ ላይ በሚደረሰው ውሳኔ መሰረት ተገቢውን ይፈጽማል፤

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው የጋራ ምክክር መድረክ ላይ ይሳተፋል፣ ስለስርጭት አፈጻጸም በየወሩ ሪፖርት ያቀርባል፤ በስብሰባ ላይ ገለጻ ያደርጋል፣ በጋራ ምክክር መድረኩ የተሰጡ መመሪያዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade Archives
መዝገብ ቤት

- የክልል እና የከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮዎች ከክልሉ ህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃ ኤጀንሲዎች ጋር በመሆን በሁሉም የስኳር ማከፋፈያ ማዕከላት የሚያቀርቡ ዩንየኖችን በመምረጥ ለንግድ ሚኒስቴር ያሳውቃሉ፣ አፈጻፀሙንም ይከታተላሉ፣

## 3.3. የዞን/ከተማ አስተዳደር ንግድ ጽ/ቤት

- በዞን/በክፍለ ከተማው የተመደበለትን የመሰረታዊ ሸቀጦች መጠን በሥሩ ለሚገኙ ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች፣ ለአገልግሎት ሰጪዎችና መንግሥታዊ ተቋማት ይደለድላል፣ ያሳውቃል፣ ይከታተላል፣

- የወሩን የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦትና ስርጭት አፈጻጸም ለክልል ንግድ ቢሮ ሪፖርት ያቀርባል፤

- በዞኑ/ከተማ አስተዳደሩ የሚያከፋፍሉ ሸማች ህ/ስ/ማ፣ ችርቻሮ ነጋዴዎችና ዳቦ ቤቶችን በተወሰነለት ቁጥር መጠን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ይመርጣል፤

- የቸርቻሪ ነጋዴዎች የመግዣና የመሸጫ ዋጋ በተወሰነው መሰረት መፈፀሙን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤

- የአስመጪው ወይም የህ/ስ/ማ/ዩንየኖች መጋዘን በር ዋጋን መሰረት በማድረግ የችርቻሮ ዋጋ በተወሰነው መሰረት መፈጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

- አስመጪው/ዱቄት ፋብሪካ የተቀበሉትን መሰረታዊ ሸቀጦች ትስስር ለተፈጠረላቸው ችርቻሮ ነጋዴዎች/ማህበራቶች/፣ ዳቦ ቤቶች እና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ስለማስራጨታቸው የሚገልፅ ማረጋገጫ ክሊራንስ/ደብዳቤ/ እያረጋገጠ በየወሩ ለአስመጪ ድርጅቶች ያሳውቃል፤

- የሸቀጦች ስርጭት በወቅቱ ለየዞኖቹ መድረሱን ያረጋግጣል፣ ችግር ካለም በክልል ደረጃ ለሚቋቋመዉ ግብረ ሀይል በፅሁፍ ያሳውቃል፣ መፍትሄም በፍጥነት እንዲሰጥ ያደርጋል፤

- የሽቀጥ ስርጭቱ በታቀደውና በግልጽነት ለህብረተሰቡ መድረሱን ይከታተላል፤ ይገመግማል፣ ከተቀመጠው አቅጣጫ ውጪ በሚንቀሳቀሱት ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

- ከክልል ግብረ ሀይል ጋር በመደበኛነት በጋራ ይገመግማል፣ ልምድ ይለዋወጣል፣ ችግሮችን እያየ የመፍትሄ አቅጣጫ ይሰጣል፤

- በአጠቃላይ ስለስርጭቱ ከሚመለከታቸው መረጃዎችን በማሰባሰብ በቂ ትንተና ያደርጋል፣ የተከሰቱ ችግሮች ላይ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

- በዚህ መመሪያ በሚሸፈኑ ሸቀጦች ክምችት ስርጭት ቁጥጥርና ሌሎችም መሰል ተግባራት በተመለከተ አስፈላጊውን ያደርጋል፤

- ዩንየኖች በየማዕከላቱ የሚያቀርቡትን ስኳር ምርት ለሸማች ህብረት ስራ ማህበራት፣ ኢትፍሩት ወይም ከችርቻሮ ነጋዴዎች ጋር በማስተሳሰር ተፈፃሚ ያደርጋሉ፣

## 3.4. የወረዳ ንግድ ጽ/ቤት

- በዞኑ/ከተማ አስተዳደሩ የተመደበለትን የመሰረታዊ ሸቀጥ መጠን በወረዳው ለሚገኙ ሸ/ህ/ስ/ማህበራትና ቸርቻሪ ነጋዴዎች ይመድባል፣ ለዞን/ክፍለ ከተማ ያሳውቃል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

- በወረዳው/ከተማ አስተዳደሩ በቂ ቁጥር ያላቸውን ቸርቻሪ ነጋዴዎችን /ማህበራቶች/፣ ዳቦ ቤቶችን ለህብረተሰቡ ተደራሽነታቸው ከግምት በማስገባት ይመለምላል ያሰማራል፤

- የመሰረታዊ ሸቀጥ ቸርቻሪ ነጋዴዎችንና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ከአስመጪ ድርጅቶች እና ከህብረት ስራ ማህበራት ዩንየኖች ጋር ትስስር ይፈጥራሉ፤

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

- በየወሩ የመሰረታዊ ሸቀጥ አቅርቦትና ስርጭት አፈጻጸም ሪፖርት ለዞኑ/ለከተማ አስተደደሩ ንግድ ጽ/ቤቶች ያደርጋል፣

- በወረዳው/ከተማ አስተዳደሩ የተመደበላቸው የመሰረታዊ ሸቀጥ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ተደራሽ መሆኑን በቅርብ ይከታተላል፣ ለሚከሰቱ ችግሮችም አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

- በወረዳው/በከተማው አስተዳደር ህብረተሰቡን በተደራጀ አኳኋን ከተመረጡ ቸርቻሪዎችና ሸ/ህ/ስ/ማ ጋር (በ1 ለ5 ) እና መሰል አመቺ አደረጃጀቶች በመጠቀም ትስስር በመፍጠር አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

- ሸማቹ ህብረተሰብም በተቀመጠው የዋጋ ተመን መሰረት ከህብረት ስራ ማህበራት፣ ከኢ.ትፍሩት እና ችርቻሮ ነጋዴዎች እየገዛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
- የመሰረታዊ ሸቀጥ ቸርቻሪ ነጋዴዎች ከአስመጪ/አቅራቢ ድርጅት ማዕከላት ርቀው በሚገኙ ወረዳዎች ቸርቻሪ ነጋዴዎች እርስ በራሳቸው ተደራጅተውና ተወካክለው ለተጠቃሚዎች ምርቱን እንዲያቀርቡ ወረዳው ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

### 3.5. የመንግስት የልማት ድርጅቶች

#### 3.5.1. የስኳር ኮርፖሬሽን

- በኮርፖሬሽኑ መጋዘኖች የሚገኝ የስኳር መጠን እንቅስቃሴ መረጃ ይይዛል፣ በየሳምንቱ መረጃዎቹን ለሚንስቴሩ በጽሁፍ ያሳውቃል፣

- ኮርፖሬሽኑ ያከናወነውን የሽያጭ መጠን በየክልሉ በመለየት በየወሩ ለሚንስቴሩ በጽሁፍ ያሳውቃል፣

- ከሚንስቴሩ ጋር በመሆን የአገሪቱን የስኳር ፍላጎትና የአገር ውስጥ አቅርቦት በመለየትና ከውጭ ሊገዛ የሚገባውን የስኳር መጠን ይለያል፣

- በአገር ውስጥ ምርት አቅርቦት ማነስ ምክንያት በሚንስቴሩ በሚቀርበው የውጭ አገር ግዥ ዕቅድ መሰረት ስኳር ገዝቶ ወደ አገር ውስጥ በወቅቱ እንዲገባ ያደርጋል፣ ይህንኑ ለሚኒስቴሩ በጽሁፍ ያሳውቃል፣

- ያጋጠሙትን ችግሮች ጊዜ ሳይወስድ በጽሁፍ ለሚንስቴሩ ያሳውቃል፣

- ሚኒስቴሩ በሚወስነው ዋጋ መሰረት ለክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በህብረት/ስ/ማ/ዩንየኖች አማካኝነት በሚቀርብለት ኮታ መሰረት ስኳርን ያሰራጫል፣ አፈፃፀሙን በጋራ በቅርቡ ይከታተላል፣ ስለአፈፃፀሙ የፅሁፍ ሪፖርት ለሚኒስተሩ ያቀርባል።

2.1.1. የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት

- ወርሃዊ የስንዴ ግዥ እና ሽያጭን ዕቅድ ያዘጋጃል፣
- በመንግስት በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ስንዴ ከውጭ ሀገር ይገዛል፣ ያጓጉዛል፣ ያከማቻል፣

- ከሚኒስቴሩ በሚላክለት ኮታ መጠን እና የመሸጫ ዋጋ መሰረት ስንዴን በክልል ተመራጭ ለሆኑ የዱቄት ፋብሪካዎች፣ የሸማች ህ/ስራ/ማህበራት ያሰራጫል። ስለ አፈፃፀሙም መረጃ በመያዝ በየወሩ እና በተፈለገው ጊዜ ሪፖርት ለሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ያሳውቃል፣

- በመጋዘን የሚገኝ የስንዴ ክምችት መረጃ በየጊዜው ይይዛል፣ ይህንኑ በፅሁፍ ለሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ያሳውቃል፣

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

- ድርጅቱ በተዋረድ በሚዋቀሩ ግብረ ሃይል ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ይሳተፋል፣ በግብረ ሃይሉ ሲጠየቅም ተገቢውን መረጃ ያቀርባል፣

3.5.2. የህብረት ስራ ማህበራት ዩንየኖች/የግል አስመጪ ድርጅቶች/አቅራቢ ድርጅቶች

- መንግስት በሚወስነው መሰረት ከውጭ እንዲገዙ ውሳኔ የተሰጣቸውን ሸቀጦች በወቅቱ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባል፤
- ለየክልሉቹ በተመደበው የመሰረታዊ ሸቀጦች ኮታ መሰረት ሸቀጡ በወቅቱ ወደ ማሰራጫ ማዕከላት እንዲደርስ ያደርጋል፣

- የድርጅቱ ቅርንጫፍ ማዕከላት በሚገኙበት ከተማዎች ወይም ዞኖች ወይም ወረዳዎች አግባብነት ባለው ግብረ - ሃይል ኮሚቴ ውስጥ ይሳተፋል፣ መረጃ ሲጠየቅም ያቀርባል፣

- የፓልም የምግብ ዘይትና ስኳር ግዢ፣ ሽያጭና ክምችት መረጃ ይይዛል፣ ስለ አፈፃፀሙም መረጃ በማጠናከር የተሟላ ሪፖርት ሳምንታዊ ሪፖርት በፅሁፍ ለሚኒስተሩ ያቀርባል፣

- መንግስት የፓልም የምግብ ዘይት እና ስኳር ለማስመጣት፣ ለማከፋፈልና ለማሰራጨት ባወጣው የአሰራር መመሪያ፣ በዘረጋው ስርዓት፣ የዋጋ ተመንና የትርፍ ህዳግ ምጣኔ፣ ድልድልና የማከፋፈያ አካባቢዎች የመስራት ሀላፊነት አለባቸው፣

- የፓልም የምግብ ዘይት ግዢ በሚፈጽምበት ጊዜ ምርቱ የኢትዮጵያን አስገዳጅ ደረጃ ማሟላቱን ያስፈትሻል፣ ጥራት የሌላቸውን ምርቶች ለህብረተሰቡ ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደርጋል፣

- የፓልም የምግብ ዘይት እና ስኳር እንዲያሰራጩ በተመደቡላቸው ክልል/ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ ሁሉም ዞኖች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የማሰራጫ መጋዘኖች፣ የግዥና የሽያጭ ሠራተኞችና ማስፈፀሚያ ሀብት ሟሟላት ይጠበቅባቸዋል ፣

- የፓልም የምግብ ዘይት እና ስኳር ግዥ፣ ክምችትና ክፍፍልን የተመለከተ መረጃ ይይዛሉ፣ መረጃውንም ለሚንስቴር መስሪያ ቤቱ እና ለክልል/ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮዎች የጽሑፍ ሪፖርት በየወሩና አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ያቀርባሉ፣

- የክልል/የዞን/ከተማ አስተዳደር የሚገኙ ቸርቻሪ ነጋዴዎች ወይም ሸማች/ህ/ስ/ማ በየዙሩ ያነሷቸውን የፓልምየምግብ ዘይት እና ስኳር መጠን በአግባቡ ለህብረተሰቡ ማሰራጨታቸውን የሚያሳይ ክሊራንስ/ደብዳቤ/ ከክልል/ከተማ አስተዳደር ወይም እነሱ ከሚወክሏቸው አካላት መቅረባቸው በማረጋገጥ ትስስር ለተፈጠረላቸው ቸርቻሪ ነጋዴዎች ወይም ሸማች/ህ/ስ/ማ እንዲሁም መንግስታዊ ተቋማቶች የማከፋፈል ኃላፊነት አለባቸው፣

- ማንኛውም በዚህ ስራ ላይ ተሳታፊ የሆነ አስመጪ የማከፋፈል ስራውን ማቋረጥ ከፈለገ ለሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ከማቋረጥበት ጊዜ ከ 3 ወር በፊት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

- አስመጪዎች/አቅራቢዎች እንዲያከፋፍሉባቸው ተወስኖ ከሚሰጣቸው የማከፋፈያ ማዕከላት ውጭ ማከፋፈል፣ ማዕከላቱን ወደ ሌላ የማከፋፈያ ከተሞች/ዞኖች/ወረዳዎች ማዛወር የመሸጫ ጭማሪ ማድረግ አይችሉም፡፡ ማዕከላቱን መቀየር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ማዕከሉ የሚገኝበት የክልሉ/ከተማ ንግድ ቢሮና ሚንስትር መስሪያ ቤቱ ቀርቦ ውሳኔ ሲሰጥበት ብቻ ይሆናል፤

- ማንኛውም አስመጪ/አከፋፋይ/አቅራቢ ምርቱን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ ዞኖች የማሰራጫ ማዕከላት መክፈት ይኖርበታል፤

- ስኳር ስርጭትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት (አለ በጅምላ) ቅርንጫፍ ባልከፈተባቸው የክልል እና የከተማ አስተዳደር ከተሞች ውጪ የህብረት ስራ ማህበራት ዩንየኖች በቀጥታ ከተመደቡበት ስኳር ፋብሪካዎች የሚመደብላቸውን ኮታ በመውሰድ ለህብረት ስራ ማህበራቶች፣ ኢትፍሩት፣ ችርቻሮ ነጋዴዎች፣ ለተፈቀደላቸው አገልግሎት ሰጪ ማዕከላት እና መንግስታዊ ለሆኑ እና ላልሆኑ ተቋማት ያቀርባሉ፡

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዛገብ ቤት

- የህብረት ስራ ማህበራት ዩንየኖች/ዘይት አስመጪ ድርጅቶች የስኳርና ዘይት ስርጭቱን ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ በየቦታው የማሰራጫ ቅርንጫፎችን መክፈት ይኖርባቸዋል፡፡

3.6. የዱቄት ፋብሪካዎች

- ከክልሉ ንግድ ቢሮ በተመደበላቸው ስንዴ ወርሃዊ ኮታ መሰረት ከተመደቡበት የስንዴ ማከማቻ ምዕከት ግዢ ይፈጽማሉ፤

- ዱቄት ፋሪካዎች እንዲሸጡላቸው በጽሁፍ ብቻ ለተመደቡላቸው ዳቦ ቤቶች እና ዳቦ ጋጋሪዎች፤ ሸማች ህብረት ስራ ማህበራት ዩንየኖች፤ ሸማች ህብረት ስራ ማህበራትና ለመንግስት ተቋማት ያሰራጫሉ፤

- ዱቄት በመንግስት በተተመነው የፋብሪካ በር ላይ ዋጋ መሰረት ሽያጭ ያከናውናሉ፤

- እያንዳንዱ ፋብሪካ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን ጨምሮ ለማን ምን ያህል እንደሸጠ በግልጽ የሚያሳይ ደረሰኝና መዝገብ በማዘጋጀት መረጃ ይይዛሉ፤

- ስንዴን በጥሬው መሸጥ ወይም ተበላሽቶብናል ወይም ሌላ ምክንያት በመፍጠር ለሌላ ፋብሪካ አሳልፎ መስጠት አይችሉም፤

- የቀጣዩን ጊዜ ኮታ ለመውሰድ ቀደም ሲል ወስዱትን ስንዴ ፈጭተው በተገቢው መንገድ ስለመሸጣቸው ማረጋገጫ ከክልል ንግድ ቢሮ ወይም ቢሮው ከሚወክለው አካል ማስረጃ ወይም ማረጋገጫ ማምጣት አለባቸው፤ ይህ ካልሆነ ቀጣዩን ስንዴ እንዲገዙ አይፈቀድላቸውም፤

- ዱቄት ፋብሪካዎች በሚገኙባቸው ከተማዎች/ወረዳዎች ምንም አይነት ጅምላ አከፋፋይ ሳይኖር ትስስር ለሚደረግላቸው ሸ/ህ/ስ/ማ ወይም ዳቦ ቤቶች በቀጥታ ምርቱን ያደርሳል፤

## 3.6.1. የመሰረታዊ ሸቀጦች ችርቻሮ ነጋዴዎች/የሸማች ህብረት ስራ ማህበራቶች

- ከአስመጪ/አቅራቢ ድርጅቶች በሚገኙባቸው አካባቢዎች የተመደበላቸውን መሰረታዊ ሸቀጥ ወቅቱን ጠብቀው በመረከብ በተቀመጠላቸው የትርፍ ህዳግ መሰረት ወረዳው/ከተማ አስተዳደሩ ትስስር ለፈጠረላቸው ተጠቃሚ ህብረተሰብ ማከፋፈል አለባቸው፣
- የስርጭት/ሽያጭ እንቅስቃሴቸውን በተመለከተ ለወረዳ/ከተማ ንግድ ጽ/ቤት ማሳወቅ አለባቸው፣
- ዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸዉን ሸቀጦችን መደበቅ እና ያለ አግባብ ማከመቸት አይችሉም
- ስለሽያጫቸዉ መረጃ ይይዛሉ፣ በተቆጣጣሪ ቢሮዎች ወይም ጽ/ቤቶች መረጃ ሲጠየቁም ያቀርባሉ፣
- በስራቸው ለሚፈጠርላቸው በ1 ለ5 እና መሰል የስርጭት አደረጃጀት ስርዓት የተጠቃሚዎች ትስስር መሰረት የተረከቡትን ሸቀጥ ማሰራጨት ይጠበቅባቸዋል፤

## 3.5.6. የህብረት ስራ ኤጀንሲዎች

- በየክልሉ ያሉ የሸማቾች ህብረት ስራ ማኅበራ ወይም ዩኒየን አቅም በመገምገም ሙያዉ ድጋፍ ያደርጋል፣
- በግብረ ሃይል አባላቱ በስብሰባው ላይ በሚወሰኑ ጉዳዮችና በሚሰጡ መመሪያዎች መሰረት የሸማች የህብረት ስራ ማህበራት ወይም ዩኒየኖችን አቅም ያንጻል፡፡
- ከስራ ድርሻው አንጻር የሸማቾች ህብረት ስራ ማኅበራ ወይም ዩኒየኖችን በሸቀጦች ስርጭት የሸማቹን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፣

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

- የህብረት ስራ ማህበራቶች/ዩንየኖች መሰረታዊ ሸቀጦችን ወደ ማቅረብና እና ማከፋፈል ስራ እንዲገቡ ከፋይናንስ ተቋቋማት የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ የመደገፍ፣ የአደረጃጀትም ሆነ የአቅም ግንባታ ስራ በመስራት ብቁ የሆኑትን በመመልመል ለንግድ ሚንስትር በማቅረብ ወደ ንግዱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያግዛል፤

3.5.6. ዳቦ ቤቶች

- ከዱቄት ፋብሪካዎች የገዙትን ዱቄት በተተመነው መጠን ልክ ዳቦ ይጋግራሉ፤

- በማንኛውም ምክንያት የገዙትን ዱቄት ለሌላ ወገን በስጦታም ይሁን በሽያጭ ማስተላለፍ አይችሉም፣

- የሚጋግሩት ዳቦ ለሸማቹ እንዲሸጥ ከሚፈለገዉ ባለ 100፣200፣300 ግራም ዉጭ በማስበለጥ ወይም በማሳነስ ከዋጋ ተመኑ በላይ የመሸጥ ተግባር መፈፀም አይቻልም፣

- ዳቦ ለመጋገር የገዙትን ስንዴ ወደ ጣፋጭ ምግቦች ወይም ወደ ሌላ የዋጋ ቁጥጥር የማይደረግባቸዉ የዱቄት ዉጤት ምግቦችን ለማምረቻነት ማዋል አይችሉም፣

- ዳቦ ቤቶች ጋግረዉም ሆነ ከዳቦ ጋገሪዎች ገዝተዉ የሚሸጡት ዳቦ በየከተሞቹ በተተመነላቸው ዋጋ እና መጠን ልክ ለሸማቹ ይሸጣሉ፣

# ክፍል አራት

## 4. የዋጋ ትመና የአስመጪዎች፣ የአከፋፋዮች፣ የቸርቻሪ ነጋዴዎች የትርፍ ህዳግ ምጣኔ አወሳሰን እንዲሁም የአመራረጥ መስፈርቶች

### 4.1. የዋጋ ትመናና የትርፍ ህዳግ ምጣኔ አወሳሰን

- ሚንስትር መስሪያ ቤቱ የአለም የመሰረታዊ ሸቀጦች ዋጋን መሰረት በማድረግ የአስመጪዎች፣ የህ/ስ/ማ/ዩንየኖች፣ ቸርቻሪ ነጋዴዎችን የመሸጫና የትርፍ መጠን እየሰራ ለተጠቃሚዎችና ለህብረተሰቡ በህዝብ ማስታወቂያ ያሳውቃል።

- ሚንስቴር መ/ቤቱ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሸቀጡን ዋጋ ለመተመን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከአስመጪዎች/አቅራቢዎች/ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት መረጃ ያሰባስባል አሰራሩንም በግልፅነት አሰራር ተመስርቶ በመስራት ያሳውቃል፣

- አስመጪዎች የአለም የመግዣ ዋጋን መሰረት በማድረግ ይገዛሉ፣ ተመሳሳይ መጠን ያላቸው ማሽኒያዎች በአማካኝ ዋጋ የመግዛትና በሚንስቴር መ/ቤቱ የሚጠየቁትን መረጃዎች፡-
  - ✓ ሸቀጡ የተገዛበት ሀገር- የአምራች ድርጅት ስም እና ቻምበራይዝ የሆኑ ኢንቮይሶች፣
  - ✓ ምርቱ የተጓጓዘበት የትራንስፖርት ድርጅት ዋጋ፣
  - ✓ ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

- አስመጪዎች በመካከላቸው ውድድር እንዲኖር ከአለም የመግዣ ዋጋና አማካኝ የፓኬጂንግ ዋጋ በታች በመቀነስ በሚስትር መ/ቤቱ ከሚተመነው የመሸጫ ዋጋ በታች መሸጥ፣ ማቅረብ ይችላሉ፣

- አስመጪዎች በሚንስቴር መ/ቤቱ ከተቀመጠው የመሸጫ ዋጋ በላይ መሸጥ አይችሉም፣

- የቸርቻሪ ነጋዴዎች በሚንስቴር መ/ቤቱ ከተተመነው የመሸጫ ዋጋና ትርፍ መጠን በላይ መሸጥና ማከማቸት የተከለከለ ነው፡፡
- አስመጪዎችና ቸርቻሪ ነጋዴዎች ሚንስቴር መ/ቤቱ በሚያወጣው የዋጋ ተመንና የትርፍ ህዳግ ምጣኔ ላይ ቅሬታ ካላቸው ለሚንስቴር መ/ቤቱና ለክልል/ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮዎች ከነበቂ ምክንያት በፅሁፍ ማቅረብና ምላሽ የማግኘት መብት አላቸው፣

➢ የትርፍ ህዳግ ፓልም የምግብ ዘይትን በተመለከተ
  - ✓ አስመጪ /አቅራቢ ድርጅቶች/ ፓልም የምግብ ዘይትን ጅቡቲ የደረሰበት ዋጋ ላይ የ3 በመቶ የትርፍ መጠን እንዲያገኙ ይደረጋል፡

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

- ✓ ቸርቻሪ ነጋዴች ፓልም የምግብ ዘይትን ከአስመጪ ድርጅቶች የገዙበትን ዋጋ 4 በመቶ ጨምረው ለሸማች ህብረተሰብ መሸጥ አለባቸው፡፡

➢ የትርፍ ህዳግ ስኳርን በተመለከተ

- ✓ አስመጪ /አቅራቢ ድርጅቶች/ ከስኳር ኮርፖሬሽን የገዛበትን ዋጋ ላይ የ1.5 በመቶ የትርፍ መጠን እንዲያገኙ ይደረጋል፤
- ✓ ቸርቻሪ ነጋዴች ስኳርን ከአቅራቢ ድርጅቶች ከገዙበት ዋጋ ላይ 6 በመቶ ጨምረው ለሸማች ህብረተሰብ መሸጥ አለባቸው፡፡

➢ የትርፍ ህዳግ ስንዴ ዱቄት በተመለከተ

- ✓ በየደረጃው ለሚተመነው የዋጋ ግንባታ ለዱቄት ፋብሪካዎች 3.7 በመቶ፤
- ✓ ለዳቦ ቤቶች ደግሞ የ2.31 በመቶ
- ✓ ለሸማች ህብረት ስራ ማህበራት/ለቸርቻሪ ነጋዴዎች 5 በመቶ ትርፍ ህዳግ ይያዝላቸዋል፡፡

- ዳቦ ዋጋ ተመን በተመለከተ
  - ✓ 100 ግራም ዳቦ ዋጋ አንድ ብር ከሰላሳ ሳንቲም (1.30)
  - ✓ 200 ግራም ዳቦ ዋጋ ሁለት ብር ከሃምሳ አምስት ሳንቲም (2.55)
  - ✓ 300 ግራም ዳቦ ዋጋ ሦስት ብር ከሰማንያ ሳንቲም (3.80) ይሆናል፡፡
  - ✓ ከከተማው ወደ ሌላ የወረዳ ከተሞች ዱቄት ለማጓጓዝ የትራንስፖርት የመጫኛና ማውረጃ ወጪን ታሳቢ በማድረግ የዳቦ ዋጋ በክልል ንግድ ቢሮዎች ይተመናል፡፡

- የዱቄት ፋብሪካዎች የዱቄት ዋጋ ግንባታ የሚሰላው የስንዴ መግዣ ዋጋ ላይ የትራንስፖርት፣ የመጫኛና ማውረጃ ወጪዎችን ብቻ በማካተት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከተለያዩ ማከማቻዎች ከሚወሰደው የስንዴ መጠንና የቦታ ርቀት ጋር በተያያዘ የሚፈጠረውን ተደጋጋሚ የዋጋ ክለሳ ሥራ ለማስቀረት ሲባል የየማዕከላቱ ርቀት ከግምት ውስጥ በማስገባት አማካይ ትራንስፖርት ወጪ ተሰልቶ በዱቄት ዋጋ ግንባታ ላይ አስቀድሞ እንዲካተት በማድረግ የተመራጭ ፋብሪካዎች መሸጫ ዋጋ በክልል ንግድ ቢሮዎች ይዘጋጃል፡፡

## 4.2. የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪ/አቅራቢ /ድርጅቶችን አመራረጥ በተመለከተ

- በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከክልል ከተማ እስከ ወረዳ ድረስ አስመጪ/አቅራቢ ድርጅት ለጅምላ አከፋፋይ የተሰጠውን ሙሉ ሀላፊነት ተክተው ይሰራሉ፤ ይህ ማለት በየትኛውም ቦታዎች በመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ላይ ጅምላ አከፋፋዮች ተሳታፊ አይሆኑም፤

- በዘርፉ ለመሰማራት የሚያስችላቸው የፀና የንግድ ፍቃድ፣ ሀብትና አቅሙ ያላቸው፣

- ለፓልም የምግብ ዘይት በሀገር ውስጥ የፓልም የምግብ ዘይት የአምራች ኢንዱስትሪ ወይም ከሀገር ውስጥና ከውጭ ባለሀብቶች በጋራ መገንባት የጀመረ መሆን አለበት፤

- የሕብረተሰቡን ጥቅም እና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠን ሸቀጦች በማቅረብና በማሰራጨት ልምድ ያላቸው፣

- የሀገሪቱን ፈጣን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሊያፋጥኑ በሚችሉ ዘርፈ ብዙ የኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ ተሳታፊ የሆኑ፤

- በፓልም የምግብ ዘይት ማስመጣትና ማከፋፈል ውስጥ አቅሙና የቀደመ ልምድ ያላቸው፣ ሚኒስትሩ ካመነ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሊመለምላቸው ይችላል፡፡

- በሀገሪቱ በኤክስፖርት ስራ የተሰማሩና የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ውጤታማ የሆኑ እና በማስመጣት በስራው ለመሰማራት ፈቃደኛ የሆኑ ላኪዎች እንደ አስፈላጊነታቸው ሊሳተፉ ይችላሉ፣

- በስኳር አቅርቦት ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ አካላት የህብረት ስራ ማህበራት ዩንየኖች፣ የኢትዮጵያ የንግድ ድርጅት (አሰ በጅምላ) እና እንደአስፈላጊነቱ የህዝብ የልማት ድርጅቶች ይሆናሉ፤

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade Archives
መዝገብ ቤት

## 4.3. የመሰረታዊ ሸቀጦች ቸርቻሪ ነጋዴዎች፣ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት እና ዳቦ ቤቶች መመልመያ መስፈርት በተመለከተ

- በዘርፉ ለመሰማራት የሚያስችላቸው የፀና የችርቻሮ ንግድ ፈቃድ ሀብትና አቅሙ ያላቸው፣
- ባለፉት ዓመታት በንግድ ስራ እንቅስቃሴው መልካም ስነ ምግባር ያለው/ላት፣ በንግድ ወይም በታክስ ማጭበርበር ያልተከሰሰ ወይም ያልተቀጣ፣
- ለመሰረታዊ ሸቀጦች ክፍፍልና ስርጭት በተዘረጋው ስርዓትና በሚወሰነው የዋጋ ተመንና የትርፍ ህዳግ መሰረት ለመስራት ፈቃደኛ የሆኑ፣
- ለመመሪያው ተፈፃሚነት የሚቀመጡ ተጨማሪ መስፈርቶችን የሚያሟላ፣
- በየአካባቢያቸው ነዋሪዎች (የሸቀጦቹ ተጠቃሚዎች) በታማኝነትና አገልጋይነት የተመሰከረላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፣
- እንዲያከፋፍሉ ለተመደበላቸው ኮታ በቂ የመስሪያ ካፒታል ያላቸው መሆን አለባቸው፣
- ዳቦ አምራቾችን ብቻ በተመለከተ ጥራት፣ብቃትና ንፅህናው የተጠበቀ የዳቦ ምርት ሊያመርት የሚችል የመጋገሪያ ማሽን ፣ንፅህናው የተጠበቀ በቂ የመጋገሪያ ቦታ እና የመሸጫ ቦታ እንዲሁም ዲጅታል ሚዛን ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል፣

## 4.4. የዱቄት ፋብሪካዎች መመልመያ መስፈርት በተመለከተ

- በዘርፉ ለመሰማራት የሚያስችላቸው የፀና የችርቻሮ ንግድ ፈቃድ ሀብትና አቅሙ ያላቸው፣
- ባለፉት ዓመታት በንግድ ስራ እንቅስቃሴው መልካም ስነ ምግባር ያለው/ላት፣ በንግድ ወይም በታክስ ማጭበርበር ያልተከሰሰ ወይም ያልተቀጣ፣

- ለመሰረታዊ ሸቀጦች ክፍፍልና ስርጭት በተዘረጋው ስርዓትና በሚወሰነው የዋጋ ተመንና የትርፍ ህዳግ መሰረት ለመስራት ፈቃደኛ የሆኑ፣
- ለመመሪያው ተፈፃሚነት የሚቀመጡ ተጨማሪ መስፈርቶችን የሚያሟላ፣
- በየአካባቢያቸው ነዋሪዎች (የሸቀጦቹ ተጠቃሚዎች) በታማኝነትና አገልጋይነት የተመሰከረላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፣
- እንዲያከፋፍሉ ለተመደበላቸው ኮታ በቂ የመስሪያ ካፒታል ያላቸው መሆን አለባቸው፣
- የተመደበለትን የጥሬ ስንዴ ኮታ በተቀመጠለት የጥራት ደረጃ (73 በመቶ) ፈጭቶ ትስስር ለተደረገለት አካላት ለማከፋፈል ብቁ የሆነ እና የአገልጋይነት ማህበራዊ ኃላፊነት የሚሰማው ብሎም ከኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት የፀዳ ፋብሪካ ፣

## 5. ተጠያቂነትን በተመለከተ

- በማንኛውም መንገድ ሸቀጦችን የደበቀ፤ ያለአግባብ ያከማቸ፤ ከተመደበለት ኮታ ውጪ ያሰራጨ፤ ከተፈቀደለት ዳቦ ቤት ወይም ቦታ ውጪ የሸጠ፤ የምርቱን የክብደት መጠን ያሳነሰ፤ ከመጠን በላይ የሸጠ፤ ለሚመለከተው አካል ትብብር ያላደረገ ሰው፤ የሚመለከተው አካል ከሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ በወንጀልና በፍትሐብሔር ህግ ተጠያቂ ይሆናል፣
- ከተመደበለት ክልል ውጪ በህገወጥ መንገድ ሲያንቀሳቅስ ወይንም በቂ ማስረጃ የሌለው የመሰረታዊ ሸቀጥ ምርት በተያዘበት ክልል ተወርሶ ሽያጩ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል፤
- የቸርቻሪዎች ወይም የሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበራት የተሰጣቸውን ሸቀጥ ያላአገባብ በመደበቅና በማከማቸት እንዲያሰራጩላቸው ለተመረጡ ንግድ ድርጅቶች ወይም ማኅበራት ሳይሆን ለሌላ አካል ሸጠውና አሰራጭተው ቢገኙ የሚመለከተው አካል ከሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ በወንጀልና በፍትሐብሔር ህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

- የዱቄት ፋብሪካዎች የገዙትን ስንዴ ፈጭተው በትስስር ለተፈጠረላቸው ዳቦ ቤቶች ወይም የጅምላ አከፋፋዮች ከማሰራጨት ውጪና ከተተመነው ዋጋ በላይ ሲሸጡ ቢገኙ የሚመለከተው አካል ከሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ በወንጀልና በፍትሐብሔር ህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

- ስንዴ ገዝተው ለህብረተሰቡ እንዲያሰራጩ የተመረጡ የኅብረት ስራ ማህበራት ወይም ዩኒዮኖች ለሸማቹ በተገቢው መጠንና ዋጋ በመሸጥ ፋንታ አስበልጠው ቢሰጡ፣ ያለአግባብ ደብቀውና አከማችተው ቢገኙ የሚመለከተው አካል ከሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ በወንጀልና በፍትሐብሔር ህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

- ለሚመለከተው መንግስታዊ አካል በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳያሳውቅ ስራውን ያቋረጠ የሚመለከተው አካል ከሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ በወንጀልና በፍትሐብሔር ህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

- ሸቀጦቹን ያለ ህጋዊ ደረሰኝ የሸጠ ወይም የገዛ እና የዋጋ ተመናቸውን በመቸርቸሪያ መደብሮች በግልጽ በወረቀት ለጥፎ ያላሳወቀ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፣

- ሌሎች ህግ የመተላለፍ ተግባራትን ፈፅሞ ሲገኝ በሀገሪቱ ህጎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፣

- በዚህ መመሪያ ላይ ሀላፊነት የተሰጣቸው በየደረጃው የሚገኙ የመንግስት ተቋሞች በመመሪያው መሰረት ኃላፊነታቸውን ባይወጡ አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናሉ፡

## 6. ቅሬታ አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ

- ማንኛውም አስመጪ/አቅራቢ/ድርጅት/ዱቄት ፋብሪካ/ በዋጋ ትመናና የትርፍ ህዳግ ግንባታ፣ በአቅርቦትና ክፍፍልን በተመለከተ ቅሬታ ካለው ለሚንስቴር መስሪያ ቤቱ የኢንስፔክሽን እና ሬጉላቶሪ ዳይሬክቶሬት በፅሁፍ ማቅረብ ይችላል፣

- ዳይሬክቶሬቱ የቀረበውን ቅሬታ በ15 ቀናት ውስጥ በማጣራት በፅሁፍ ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፣

- አስመጪ/አቅራቢ/ድርጅት/ዱቄት ፋብሪካ/ ባቀረቡት ቅሬታ ላይ የተሰጣቸው ውሳኔ በቂ አይደለም ብለው ካመኑ ለሚንስትሩ ጽ/ቤት ደግመው በማቅረብ ምላሽ የማግኘት መብት አላቸው፣

- የችርቻሮ ነጋዴዎች/ሸማች/ህ/ስ/ማ//ዱቄት ፋብሪካዎች/ዳቦ ቤቶች/ በሂደቱ አሉን የሚሉትን ቅሬታዎች በክልል/በከተማ/በዞን አስተዳደር የንግድ ቢሮዎች አቅርበው ምላሽ የማግኘት መብት አላቸው፣

- ችርቻሪ ነጋዴዎች/ዳቦ ቤቶች/ በሂደቱ ያላቸውን ቅሬታዎች ለወረዳ የንግድ ጽ/ቤቶች እና ለዞንና ክፍለ ከተማ/ወረዳዎች የንግድ ቢሮዎች በየደረጃው በማቅረብ ምላሽ የማግኘት መብት አላቸው።

ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

# ክፍል አምስት

## በመመሪያ ተግባራዊ የሚሆኑ አስገዳጅ አባሪዎች

## 1. የመሰረታዊ ሸቀጦች የስርጭት ሰንሰለት

### .1.1.የፓልም የምግብ ዘይት የስርጭት ሰንሰለት



### 5.1.2. የስኳር የስርጭት ሰንሰለት




ንግድ ሚኒስቴር
Minisstrv of Trade Archives
መዝገብ ቤት

### 5.1.3. የስንዴ ዱቄት የስርጭት ሰንሰለት



5.2. የመሰረታዊ ሸቀጦች የዋጋ ግንባታ፣የመግዥና መሸጫ ተመን መግለጫ ሰንጠረዥ

5.2.1. የፓልም የምግብ ዘይት

5.2.2. የስኳር

5.2.3. የስንዴ ፣ስንዴ ዱቄትና ዳቦ

6. የተሻሩ አሰራሮች

ይህ መመሪያ ከዚህ በፊት በስራ ላይ የነበሩትን የሸቀጦች መመሪያ ሁሉ ይሽራል፡፡ እንዲሁም ከዚህ መመሪያ ጋር የሚጋጩ ሌሎች መመሪያዎች ወይም የተለመምዶ አሰራሮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ፡፡

7. መመሪያዉን ስለማሻሻል

ይህንን መመሪያ የማሻሻል ወይንም የመሻር ሥልጣን የሚንቴር መስሪያቤቱ ነው፡፡

8. <u>መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከ__2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ንግድ ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ</u>

__________2008 ዓ.ም

አሰድ ዚያድ

ሚኒስትር ዴኤታ